# አውደ ኢትዮጵያ

መጋቢት 1 2008 | የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ህጋዊ መንግሥትንና ፍትሃዊ ስርዓትን የመጠየቅ መብት አለው! | እትም 24

## ብርቱካን ትፈታ

# ቃለ መጠይቅ ከወ/ሮ አልማዝ ገብረ እግዚአባሄር ጋር -

በአቶ ደበበ እሸቱ

ይህን ቃለ ምልልስ ለማድረግ ከወ/ሮ አልማዝ ጋር በነበረኝ ቀጠሮ መሰረት ወደ ቤታቸዉ ወደ ፈረንሳይ ኤምባሲ አካባቢ የሄድኩት በቀጠሯችን ሰዓት ነበር። ዋናዉን መንገድ ለቅቄ ወደ መንደሩ ገባ ስል በአካባቢዉ ካለዉ ወፍጮ ቤት አጠገብ ወ/ሮ አልማዝ ቆመዉ ከአንዲት ሴት ጋር ወሬ ቢጤ ይዘዋል።

አጠገባቸዉ ስደርስ መኪናዬን ሳቆም «ግድ የለም እንናተ ሂዱ፣ እኔ እመጠላሁ» አሉ ። ያሉት ከቤታቸዉ ራቅ ብለዉና እየመሸም ስለነበር «መኪና ዉስጥ ገብተዉ አብረን እንሂድ» ብንልም አሻፈረኝ አሉ። እኔም «በጭራሽ አብረን እንሂድ ይግቡ ፣ ለምኑ ነዉ ?» በማለት ጠንከር ስል «አይ ቅቤ ተቀብቼ ነዉ። ደግ አይደለም ብዬ ነዉ። እባካችሁ ሂዱ እደርስባችኋለሁ» ቢሉም አሻፈረኝ ብዬ የግድ አስገብቻቸዉ አብረን ሄድን።

እዉነቱን ለመናገር አንድም የቅቤ ሽታ አልነበረምና «እሜቴ የታል ቅቤዉ ?» አልኳቸዉ። «አናቴ ጠጥቶ ጨርሶት ይሆናል» ብለዉ ወደ ቤት ይዘዉን ገቡ።

ከተም በሩን የከፈተችልን እሳቸዉም ልጄ፣ ብርቱካን እህቴ የምትላት የወንድማቸዉ ልጅ ነበረች። ሰላም ብለናት ስንዘልቅ «ፍልቅልቋ» ሃሌ በረንዳዉ ላይ ከፊሉን ደረጃ ወርዳ ትጠብቃለች። እያቷን ሰላም ብላ እኛንም ሰላም አለችን። ሃሌና እኔም አብሮኝ የሄደዉም የሺዋስ ጋር እንተዋወቃለንና እቅፍ እያደረገች ነዉ ሰላማታ የሰጠችን። ወዲያዉ ወደ ዉስጥ ገባንና አርፍ አልን።

ስለሄድንበት ጉዳይ አስቀድሞ በስልክ ያነጋገርኩዋቸዉና ጉዳዩን የሚያወቁ ቢሆንም ለማረጋገጥ ያህል በድጋሚ «በአሜሪካ ያሉ የብርቱኳ ደጋፊዎች ስለአስተዳደጓ ማወቅ ስለፈለጉ ነዉ ልጠይቅዎት የመጣሁት» ከማለቴ ወዲያዉ መልስ መስጠት ጀመሩ። ደግነቱ ቴፑ ክፍት ስለነብር ያዘልኝ እንጂ ጉድ ልሆን ነብር።

ከወ/ር አላምዝ ጋር ያደረኩትን አጭር ቃለ ምልልስ እንደሚከተለዉ አቀርቤዋለሁ።



ደበበ - ወ/ሮ አልምዝ ብርቱካን መቼ ነዉ የተወለደችዉ ?

ወ/ሮ አልማዝ - ቀኑንማ እንግዲህ እኔ ምን አወቄ። ምልክቱ ግን በጃንሆይ ጊዜ ነዉ። ምልክቱ እሱ ነዉ። እርሳቸዉ ሲወርዱ ነዉ የተወለደችዉ። ከዚያን ሰዓት ጀመሮ በአራት አመቷ የፊደል ትምህርት ገባች። በአምስተኛ አመቷ አንደኛ ክፍል ገባች። ከዚያ አንድም ጊዜ ወደቃ አታወቅም። አንደኛ አንደኛ እየወጣች ፣ እየተሸለመች እና 12ትም ያዉ በፈተናዉ 100 አገኘች ተብሎ ዩኒቨርሲቲ ገባች።

ደበበ - በአምስት አመቷ አንደኛ ክፍል ገባች ብለዉ በስንት አመቷ 8ኛ ክፍል እንደጨረሰች አልነገሩኝም።

ወ/ሮ አልማዝ - እንዴ ስምንተኛ ሳትጨርስ 12ኛ አትገባም መቼም።

ደበበ - አላነሱትም ብዬ ነዉ

ወ/ሮ አልማዝ - ጠይቀኝ እመልሳለሁ፡

ደበበ - እስከ ስምንተኛ እንዴት ነበር ትምህርቷ

ወ/ር አልማዝ - ጎበዝ ነበረች እንዳልኩህ በአምስት አመቷ 1ኛ ገባች። በቃ በየክፍሉ አንደኛ አንደኛ እየወጣች እየተሸለመች ጨረሰች። አንድም ጊዜ ወድቃ አታወቅም።

ደበበ - በአካባቢዋስ ጠባይዋ እንዴት ነበር ? ከመንደር ልጆች ጋር ትጣላ ነበር ? ተንኮል ነበራት ?

ወ/ሮ አልማዝ - ማን ? ብርቱ ? እሷ እቴ ምን በወጣት ? ከመንደሩ ልጆች ጋር ፍቅር ነበረች። ሁሉም አብረዋት ለማጥናት ነዉ የሚፈልጉት። የመንደሩ ሰዉ ሁሉ በፍቅር ነዉ የሚወዳት። ብርቱ ለፍቅር ነዉ የተፈጠረቸዉ ስልህ !

ደበበ - አስተዳደጓስ እንዴት ነበር ? አባቷስ ምን ነበሩ ?

ወ/ሮ አልማዝ - አባትዋ ወታደር ነበሩ። ብርቱ የተወለደችዉ ጡረታ ከወጡ በኋላ ነዉ። ታዲያ በዳቦ ነዉ ያደገችዉ። እንጀራ እንኳን አትወደም ነበር። በጡረታችን ተንከባከብን ነዉ ያሳደግናት።

ደበበ- ጡረታዉ ስንት ነበር ?

ጡረታችን 30 ብር ነበር። በኋላም ተመልሰን ሥራ እንደገና ስንጀመር ደሞዝ ከሁለት ወገን ነበረን።

ደበበ - ታስቸግር ነበር በልብስ በጫማ ምርጫ ?

ወ/ሮ አልማዝ- እሷ እቴ በጭራሽ። የምታስቸግረዉ እንጀራ አልበላም ብላ ነዉ። ዳቦ ትላለች። ከዚያ ዉጭ በጭራሽ አስቸጋሪ ጠባይ የላትም። አስቸግራኝም አታወቅም። አሁን ነዉ ችግር የመጣዉ። ከጎሮቤት ጠብ የላት። ፍቅር ብቻ ነበረች ። ከማንም ተጋጭታ አታወቅም። ከሁሉም ጋር ፍቅር ነዉ። 12ኛን ስትጨርስ ወንድሟ ጋር አዋሳ ሄደች። ወዲያዉ የ12ኛ ወጤት ሲመጣ አልፋለች ተብሎ ጥሯት ቶሎ ጥሯት ተባለ። አዲስ አበባ ነዉ የደረሳት ተባለ። መጣታ ገባች። ያወ አምስት አመት ተምራ በጥሩ ዉጤት አልፋ በሕግ ተመረቀች።

ደበበ- ከሚሰብሩት ጋር አብራ ትቀላቀል ነበር?

ወ/ሮ አልማዝ - እኔ እንግዲህ ሰበርኩ ብላኝ አታወቅም። ግን መቼም ....ብቻ ብዙ ጊዜ ጥፋት ቦታ አትገኝም። የአሁኑ ምን እንደሆነ አልወቅም። ጥፋት ነዉ አሉ እነርሱ ። እኔ ግን ጥፋቱ አልታይሽ እያለኝ ግራ እጋባለሁ።

ደበበ - እኔ አሁንም ቢሆን ጥፋት አላይባትም።

ወ/ሮ አልማዝ:- እነርሱ ደግሞ ጥፋት ነው አሉዋ !

ደበበ - እነርሱ ባሉት ሳይሆን እንደ እዉነቱ ።

ወ/ሮ አልማዝ- እንደ እዉነቱማ ብርቱ ጥፋት ያሉት ነገር አታወቅም። አላደገችበትም። አልኖረችበትም። አይተዋወቁም።

ደበበ - አሁንም አላጠፋችም። ጥፋት የለባትም።

ወ/ሮ አልማዝ:- ጥፋት ነዉ ብለዉ አይደል ወህኒ ያገቡብኝ።

ደበበ - የጉልባት ጉዳይ ነዉ እርሱ

ወ/ሮ አልማዝ - መቼ አሉ ? ጥፋት ነዉ ነዉ የሚሉት።

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

## አንብበው ለወገን ያሰተላልፉ

# ዝምታ ይብቃ!

## ርዕሰ አንቀጽ







አገር ሲደፈር ዝምታ፤ ወገን ሲገደል ዝምታ፤ ታጋይ ሲሰቃይ ዝምታ፤ የህዘብ ንብረት ሲዘረፍ ዝምታ ባህላችን እንዳይሆን አደራ ሊባል ይገባል።

አገራችንና ዜጎቿ ከአንድ ጉድ ወጥተን ወደ ሌላ ስንገባ፣ የተሻለ ይመጣል ሲባለ የባሰ ሲፈራረቅብን፣ ህሊና ያለው አቤት ሲል ዝም ያለው እንዳላየና እንዳልሰማ ሲሆን ምነው ወገን ይህ እኮ የግል ንግድ አይደለም የህዝብ ደህንነትና የሃገር ህልውና ነው። አቅም ካነሰ በጉልበት ካልሆነም በአንደበት ለእወነት እንቁም እንጂ።

ወያኔ ለስጋቸው «እኔ ከተመቸኝ አይኔን ግንባር ያድርገው። አልሰማሁም፤ አላየሁም አልናገርም» ብለው ድብብቆሽ የሚጫወቱትን ግለሰቦች ነገ ለወያኔ እራት ሊሆኑ ጊዚያቸውን ሲጠብቁ ፣ ለፍትህ መቆም በራስ ላይ ሲደርስ አለመሆኑን አለመንገዘብ የህሊና ድክመት ነው።

በሆነ ባልሆነው ሰበብ ማብዛትም ይብቃና፣ መደበቂያ ጉድጓድም መቆፈር ይቅርና፣ የጋራ ጉዳይ ላይ እንኳን የወያኔን ወንጀል ይቁም ማለት የዜግነት ግዴታ ብቻ ሳይሆን የሰውነትም መለኪያም ነዉ።

የሞቀበት ቤት ገብተን «ኦባማ ኦባማ» ባልንበት አንደበት ወገኖቻችን አይታሰሩ፤ የህዘብና የሀገር ንብረት በጥቂቶች አይዘረፍ፤ ተጠያቂነት ይስፈን፤ የተገደሉና የተበደሉ ፍርድ ያግኙ፤ የሀገር ህልውና ይጠበቅ፤ ወገንን ማጋጨት ይቁም፤ ህዘብ መሪዉን ይምረጥ፤ ህዝብን መደለል ይብቃ፤ በግፍ የታሰሩ ዜጎች ይፈቱ የሚሉት ጥያቄዎች የግለሰብ፤ የፖሎቲካ ፓርቲም የቡድንም ጥያቄ ሳይሆን የህዝብ የሰባዓዊ መብት ጥያቄዎች ናቸው።

ፕሬዚደነት ኦባማ እንኳን ከሃገራቸው አልፈው በአለም ላሉ ህዝባቸውን ለሚጨቁኑ አመባገነኖች ማስጠንቀቂያ ሲሰጡ ለራሳቸውም ለህዝባቸው ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለማያውቁት የሰው ልጅ ሰብዓዊ መብት መከበር ነበር። ታዲያ እኛ ለገዛ ወገኖቻችንና ለሃገራችን ጉዳይ አይናችንን ጨፍነን፤ አፋችንን ለጉመንና ጆሮችንን ደፍነን ፕሬዚደንት ኦባማ አገራቸውም ወገናቸውም ላልሆኑ ሲቆረቆሩ የሳቸው ደጋፊ ነን ማለት ከእራስ ጋር መጣላት አይሆንምን?

በአፍ ዝምታ፤ በአይን ጭፈና በጆሮ ደፈና እራሳቸው ፕሬዚዳነት ኦባማም አይመረጡም ነበር። ግዴታችንን እንወጣ።

ወያኔን ሙጥኝ ያሉ ዜጎችም በህሊና ጨለማ እየተጓዙ የአምባገነን መሳሪያ ሊሆኑ በመምረጣቸው፤ የኢትዮጵያን ህዘብ መከራና ስቃይ ለማራዘም መንግስት ይሁን፣ ነጋዴ ይሁን፣ አገር ወዳድ ይሁን፣ ከዛሬ ነገ የሚያደርገውን ለማያውቀው ቡድን ምሶሶ ሆነው ሲያገለግሉና ሲዋሹለት ማየት ለሀገራቸውም ለወገናቸውም ለራሳቸውም ሳይሆኑ ከንቱ ሆነው ሊቀሩ እንደመረጡ መረዳት አለባቸዉ።

ዘመኑ ሁላችንንም የሚያቀራርብ ሆኖ የአለም ዜጋ ባደረገን ወቅት፤ ከተጠያቂነት የምንደበቅበት ዘመን በጠበበት ሁኔታ እነደተለመደው አማባገነንን አገልግዬ፤ አጥፍቼና የሰባዊ መብት ረግጬ እደበቃለሁ የሚል ግለሰብ ካለ ወይ ሞኝ ነው አለዚያም ቀኑ የጨለመበት ብቻ ነው።

ለጊዜው የሚፈራገጡ የአምባገነን አገለጋዮች ከተጠያቂነትና ከህዘብ ፍርድ አያመልጡም።አወጡት፣ አወረዱት፣ ደበቁት፣ ዋሹት፣ ሕዝባዊ መንግሰትና ተጠያቂነት ይኖራል።

**ዝምታ ይብቃ!!! ተጠያቂነት ይምጣ!!!**

# ከወ/ሮ አልማዝ...

ከገጽ 1 የዞረ

ደበበ - የለም ጥፋት አይደለም። ለሕዝብ ታማኝ መሆን፣ ለሕዝብ መቆም፣ የሕዝብ መብት ለማስከበር መታገል ቃልን መጠበቅ ምኑ ነዉ ጥፋቱ ?

ወ/ሮ አልማዝ - እስቲ እንግዲህ ይሁን ። እግዚአብሄርን ነዉ የምንለምነዉ። የርሱ ድርሻ ነዉ ከእንግዲህ ወዲያ - የሱ ጉዳይ ነዉ።

ደበበ- ትምህርትስ ከጨረሰች በኋላ

ወ/ሮ አልማዝ - የየካ ክፍለ ከተማ ዳኛ ሆነች በኮንትራት

ደበበ- እንዴት ነበረ ከሕዝብ ጋር ከባለጉዳይ ጋር የነበራት ስም ?

ወ/ሮ አልማዝ - በፍቅር ነበር የሚያነሷት። ይነግሩኝ ነበር። ለሰዉ ታዝናለች ይሏት ነበር። በኋላም ደግሞ ዳኝነቱን ትታ ጠበቃም ስትሆን ጥሩ ስም ነበራት። ለቸገረዉ በነጻ ትቆማለች። የቻላችሁትን ክፈሉ ትላላች። ደግ ነች። ሌሎች ጠበቆች ታዲያ ያንን ሲሰሙ ይበሳጩ ነበር። አበላሸሽብን እያሉ ይወቅሷት ነበር። እርሷ ደግሞ የተቸገሩ ጠበቃ ይጡ ወይ ትል ነበር።

ደበበ- አንድ ጊዜ ዳኛ እያለች የአቶ ስዬ አብርሃን የዋስ መብት ፈቅዳ ነበርና ያን ጊዜ ሰዉ ምን አለ ?

ወ/ሮ አልማዝ- ዉጭ ነበርኩኝ ያን እለት። ተመልሼ ቤት ስመጣ ቤት ሰዉ ብቻ ነበር። ምንድን ነዉ ስል እንዲህ እንዲህ ሆነ አሉ።

ደበበ - ምንድን ነዉ እንዲህ እንዲህ?

ወ/ሮ አልማዝ - «ለብዙ ጊዜ አለአግባብ ዋስ ተከልክለዉ የነበሩትን ስዬ የሚባሉትን (የነሱ ጓደኛ ነዉ አሉ) የዋስ መብታቸዉን ፈቀደችላቸዉ። የሕግን የበላይነት አረጋገጠች። ለሕግና ለደንቡ እንጂ ለማንም ብላ እንደማትፈርድ አሳየች።» ብለዉ ደስ ብሏቸዉ እግዚአብሄር ከአይን ያዉጣልሽ አሉኝ። ወዲያዉ ከሥራ ወጣሁኝ አለች። ደነገጥኩኝ። ምን እንሆናለን እያልኩ ሃሳብ ያዘኝ።

ደበበ-ወጥታስ?

ወ/ሮ አልማዝ - ጥብቅና ገባች። ከዚያ በኋላ ነዉ ይህን ቤት የሰራነዉ። የበፊቱን አፍርሰን ይህን ሰራን። ጥብቅና ከገባች በኋላ። አሮጌ አፍርሰን አዲስ ስንሰራ መቀመጫ አጣን።

ደበበ-ወደ ፖለቲካ ከገባችስ በኋላ ?

ወ/ሮ አልማዝ - የፖለቲካን ነገር እኔ አልወቅም። እንዲህ ያለ ነገር ጋር አትሂጅብኝም እላለሁ።

ደበበ - እርሷስ ምን አልችዎት ?

ወ/ሮ አልማዝ - ማን ? ብርቱ ? እርሷ ስቃ ዝም ነዉ። እንዲህ ነዉ እንዲያ ነዉ አትልም።

ደበበ - አሁንስ ቃሊቲ ይሄዳሉ። ይጠይቋታል። ሃሌም ትሄዳለች ?

ወ/ሮ አልማዝ - እሁድ አልደርስ እያለኝ እጠብቀዋለሁ። ለኔ ሲሆን ደግሞ ቅዳሜና እሑድ ይርቃል። በፊት ሳይታሰብ ነብር የሚደርሰዉ። አሁን ይጎተታል።

ደበበ -ብርቱኬ ስሜቷ እንዴት ነዉ ? አሁን እናንተን ስታይ ሃሌን ስታይ እንዴት ነዉ ስሜቷ ?

ወ/ሮ አልማዝ - እኛ እንዴት ሆና ይሆን ብለን እንጨነቃለን። እርሷ ደህና ነች። ኀበዝ ጠንካራ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ኢህአዲግ በህዝብ ዘንድ ያጣውን ተቀባይነት ለመመለስ ያደረገው ከንቱ ጥረት

የኢህአዲግ መንግስት ከ97 ምርጫና ግርግር በኋላ እንደሰሞኑ ያለ አጣብቂኝና በህዝብ እምነት ማጣት ገጥሞት የሚያውቅ አይመስልም፡፡ በሶማሊያ ያሰማራው ሰራዊት ለቀድሞ ‹‹አሸባሪ›› ሼህ ሸሪፍ ሼህ አህመድ የፕሬዝዳንትነት መንበሩን አስረክቦ ተመልሷል፡፡ የበጎ አድራጎትና ማህበራት ህግ በርካታ ወራትን የፈጀ እሰጣ ገባ ቢካሄድበትም ‹‹የአብዮታዊ ዲሞክራሲያችንን የልማትና የዲሞክራሲ አቅጣጫችን እንዳያዛባ ለመከላከል ሲባል›› ያለ ምንም ማሻሻያ እንዲፀድቅ ሆኗል፡፡ ከዚህ ሁሉ በባሰ የአንድነት ሊቀመንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ‹‹ህግን ጥሰው በመገኘታቸው ያለ ህግ አግባብ›› እንዲታሰሩ ተፈርዶባቸዋል፡፡

ይህ ሁሉ ድርጊት የመንግስትን ፖሊሲ ቀረፃና አተገባበር ያስገመተ፣ ህግን የናደና በህዝብ ዘንድ የነበረውን እንጥፍጣፊ እምነት እንዲያጣ አድርጎታል ኢህአዲግን፡፡ ኢህአዲግ ወትሮም በህዝብ ያጣውን እምነት ከመገንባት ይልቅ ይበልጥ እያመነመነው መምጣቱን ሰሞኑን በየመንግስት መ/ቤቱ የሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ማሳያ ናቸው፡፡

በቅርቡ የማስታወቂያ ሚንስቴርን ቦታ ተክቶ የተቋቋመውና በአቶ በረከት ስምኦን የሚመራው የኮምንኬሽን ጽ/ቤት አዘጋጅቶ ‹‹እንወያይበት›› ያለው ሰነድ ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት ጉዳዮች ያነሳል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ‹‹ጎልተው የወጡ በመሆናቸው መንግስት በትክክል አቋሙን ግልፅ ሊያደርግባቸው›› ስለሚገባ የተዘጋጀ ነው ሰነዱ፡፡

የፁሁፉ መጀመሪያ ሰራዊታችን ወደ ሱማሌ የዘመተው ‹‹በኤርትራ አቀናባሪነት፣ በሱማሌ አክራሪ ሽብርተኞች ተባባሪነትና በሀገር ውስጥ አፍራሽ ሀይሎች አማካኝነት የተደቀነብንን የሉአላዊነት አደጋ ለመግታት›› እንደነበረ ይተነትናል፡፡ ‹‹አክራሪዎቹና በነሱ ፈረስነት የተፈናጠጡ ሀይሎችን በሁለት ሰምንት ጊዜ ውስጥ አከርካሪያቸውን መስበር መቻላችን ወሳኝ ድል ነው›› ይላል ሰነዱ፡፡ ለዚህ ድል ያበቁንን ዘማቾችም በነገሌ ቦረና የማእረግ እድገት እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡ ለሰማእታቱም በሱማሌ ክልል የመታሰቢያ ሀውልት ለመገንባት የመሰረት ድንጋይ ተጥሏል፡፡

የኢህአዲግ መንግስት የራሱን ያረረ ድስት እንደጣደ ትቶ የሰው ለማማሰል መሄዱን ከሉአላዊነት ጋር አያይዞ፣ ሰራዊቱ የራሱን ህዝብ እንዲጨፈጭፍ ያደረገበትን፣ የተጠላበትንና በህዝብ ዘንድ ያጣውን እምነት (ሊጅትማሲ) ለመመለስ የተደረገ ሙከራ አድርገው ለሚቆጥሩት የፖለቲካ ተንታኞች ‹‹ያሰበውን ያላሳካ ዘመቻ›› እንደሆነ፣ ህዝቡ አሁንም በመንግስቱ እምነት እንደሌለው ይገልፃሉ፡፡

በአቶ መለስ የሚመራው መንግስት ለዚህ ምላሽ ከማዘጋጀትና ‹‹ለተጠያቂነቱ›› ተገቢ መለስ ከመስጠት ይልቅ ድርቅ ባለ አመክንዮ ህብረተሰቡን ለማሳመን እየማሰነ ይገኛል፡፡ ለመሆኑ ዘመቻው ስንት ብር ፈጀ? በሰወ የተከፈለው መስዋእትነትስ? ግቡስ ተሳክቷልን? ኢህአዲግ ለዚህ የሚሰጠው ምላሽ መንግስት ከመሆን የሚጠበቅ ቢሆንም አላደረገውም፡፡ ይልቅስ የተያዘው ‹‹የአሸባሪው አከርካሪ ተሰብሯል፣ የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ተከብሯል እመኑኝ›› ነው፡፡ በገሀድ የሚታየው ግን የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት ዋና መሪ ፕሬዝዳንት ሆነው መመረጣቸውን፣ ሰራዊታችንም ለእርሳቸው የስልጣን መንበሩን አስረክቦ መመለሱን ነው፡፡ እኚህ ሰው ማን ነበሩ? ኢትዮጵያ ላይ ጅሀድ ያወጁት ሰውዬ አይደሉምን? የዘመቻው ግብስ ይሄ ነው? ኢህአዲግ የህዝብን አመኔታ አገኛለሁ፣ የትኩረት አቅጣጫውን አስቀይረዋለሁ ብሎ በስህተት ላይ የደረበው ሌላ ስህተት ነው፡፡ ይህንንም የመንግስት ሰራተኛው እንዲቀበል እየሰበሰቡ መስበክ ሆኗል የሰሞኑ የአቶ በረከት ‹‹በረከት (ፀጋ)››

ሌላው የመወያያ አጀንዳ የበጎ አድራጎትና ማህበራትን የሚመለከተው አዋጅ ነው፡፡ ‹‹ህጉ ከመፅደቁም ሆነ ከፀደቀ በኋላ ከፍተኛ የማጥላላት ዘመቻ›› ተካሂዶብናል የሚለው ይህ ሰነድ፣ ተልእኮው የሀገራችንን ሉአላዊ ህግ ማውጣት መብት የጣሰ›› ይለዋል፡፡ ህጉ እንዳይፀድቅ የተከራከሩትም የውስጥ አርበኛ በመሆን ከውጭ በሚገባን ገንዘብ የተለያዩ ሀይሎችን ተልእኮ ማስፈፀሚያ ሊያደርጉን ያሰቡ እና በሚያገኙት ገንዘብ የውስጥ ፖለቲካችንን ለመበጥበጥ የተነሱ ናቸው ሲል ያጣጥላቸዋል፡፡ ስለዚህ? ስለዚህማ የህጉን መፅደቅ ተቀበሉ ተብለዋል ተሰብሳቢዎቹ፡፡

ይህ በንባብ ለተሰብሳቦዎቹ የሚሰማው ሰነድ በስተመጨረሻ የሚያነሳው የወ/ሪት ብርቱካንን መታሰር ተገቢነት ለማሳመን ነው፡፡ ‹‹በቅድመ ሁኔታ የተሰጣቸውን ይቅርታ ክደው ምንም አይነት የፀፀት ስሜት ስላልተሰማቸው ይቅርታው መነሳት ይገባዋል፡፡ ያልጠየቁት ይቅርታ አይገባቸውም፡፡ ጉዳዩ የተፈፀመው የህግን የበላይነት ለማስከበር ነው›› ወ/ሪት ብርቱካን የተያዙበትና ያሉበት ሁኔታ፣ የተወሰደባቸው እረምጃ ከህግ አግባብ ውጪ ነው የሚሉ ወገኖች ‹‹በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ለመግባት የሚፈልጉ ሀይሎች ናቸው፡፡ ሰፊ ዘመቻም ከፍተውብናል›› ይላል ሰነዱ፡፡ ‹‹ሊቀመንበሯ ካልተለቀቁ በሰላማዊ ሰልፍ እና የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግ እርዳታ እንዲቋረጥ እናደርጋለን፣ መንግሰትን ፋታ እናሳጣዋለን›› የሚሉትንም ይኮንናል፡፡

ወ/ሪት ብርቱካን እስካሁን በኢ-ሰብአዊ አያያዝ እንዳሉ፣ መብራት በሌለው ክፍል ውስጥ ለብቻቸው እንደታሰሩ፣ የትኛውንም የመገናኛ ብዙሀን እንዳይከታተሉ እንደታገዱ፣ ከእስረኛ ተለይተው በሰዎች እንዳይጎበኙ.....መደረጋቸውን ሁሉም ቢያውቅም የአቶ በረከት ሰነድ አንዳች ሳይል ያልፈዋል፡፡ ጠ/ሚንስትሩም ለጋዜጠኞች የተጣሰ ሰብአዊ መብት የለም ቢሉም አለመኖሩን ለማስረገጥ እስካሁን ለአለም አቀፍም ሆነ ለሀገር ውስጥ ቀይ መስቀል፣ ለሰብአዊ መብት ተሚጋቾች የሚታዩበትን ሁኔታ አላመቻቹም፡፡ የህግ አግባቦትን፣ አናቅፅትን እየጠቀሰ የተከራከረ አንድም ባለስልጣን አለመኖሩም በጉዳዩ ላይ ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ ‹‹ይቅርታ አልጠየኩም ብለዋል ስለዚህ ታሰሩ›› ከሚል መከራከሪያ ውጭ የህግ ንጥር አውጥተው ለማሳመን ከመሞከር ይልቅ ‹‹ከብረት በጠነከረ ሎጂክ›› እመኑኝ ማለታቸው ያጡትን የህዝብ አመኔታ የበለጠ የሚሸረሽር ሆኖባቸዋል፡፡

ካለፈው ሁላት ሳምንት ወዲህ ከላይ በተነሱት ነጥቦች ላይ፣ በተለይ በወ/ሪት ብርቱካን እስር ላይ የኮሙንኬሽን ጽ/ቤቱ በስብሰባና አስተያየት በመሰብሰብ ላይ ሲሆን፣ ከጥቂት የኢህአዲግ አባላት በስተቀር አንድም ሰው በሰነዱ እንደሚስማማ አልተናገረ፡፡ አብዛኛዎቹ ስብሰባዎች በዝምታና በጉርምርምታ የተሞሉ እንደነበሩ ተሰብሳቢዎቹ ይገልፃሉ፡፡ ስብሰባው አህዱ ብሎ የጀመረው ከሁለት ሳምንት በፊት በቴሌ ኮሙንኬሽን ሰራተኞች ሲሆን አንድም ገለልተኛ የሚባል ግለሰብ አስተያየት ሊሰጥ አልደፈረም፡፡ ‹‹እውነቱን እናውቀዋለን፡፡ ትርፍ መናገር ስራን ሊያሳጣ ስለሚችል መናገሩ አስፈላጊ አልነበረም›› ያለን በቦሌ ቅርንጫፍ የሚሰራ የመ/ቤቱ ባልደረባ ነው፡፡ ‹‹ሁሉም በእልህና በስሜት ቢዋጥም ተከትሎ የሚመጣውን ጣጣ የከፋ ይሆናል በሚል ለመናገር አልደፈረም፡፡››

የአቶ በረከት ጽ/ቤት በመደባቸው ሶስት ሰዎች አማካኝነት የሚደረገው ይኸው ስብሰባ ባለፈው ሳምንት መገባደጃ ላይ የተደረገው በጥራትና ደረጃዎች መዳቢ ባለስልጣን መ/ቤት ነበር፡፡ ሰራተኞቹ ላለመሰብሰብ ከማቅማማት ጀምሮ እሰጣ ገባ ውስጥ ገብተው እንደነበር የገለፁት ምንጮቻችን ‹‹የተወሰኑ ሰራተኞች ስራ ጥለን ስብሰባ አንቀመጥም›› ማለታቸውን ተናግረዋል፡፡ የቡናን ጥራትና ደረጃ በመለየት ስራ የተሰማሩት እነዚሁ ‹‹እንቢ ባይ›› ሰራተኞች በሰብሳቢዎቹ አማካኝነት ግድ ሊሰበሰቡ እንደሚገባ ቢነገራቸውም ፍቃደኛ አልሆኑም፡፡ ‹‹ቡና በአፋጣኝ ተመርምሮና ደረጃ ወጥቶለት ለሽያጭ መቅረብ አለበት፡፡ የሀገሪቱ ህልውና በቡና ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ስብሰባው ከስራችን አይበልጥም›› ብለው ቀርተዋል፡፡ የባለስልጣኑ ዳይሬክተር አቶ መሳይ ጋር ሄደው ስለሁኔታው ቢያስረዱትም ‹‹እኔ በዚህ ጉዳይ ላይ አያገባኝም፣ አይመለከተኝም›› መባላቸውን የሚገልፁት እነዚሁ ሰራተኞች በራሳቸው ውሳኔ ከስብሰባው ቀርተዋል፡፡

ስብሰባውን የታደሙ ሰራተኞች በበኩላቸው የተነበበላቸውን ከመስማት በቀር አንዳችም ቃል ለመናገር ፍቃደኛ እንዳልነበሩ ነው የሚናገሩት፡፡ ሰብሳቢዎቹም ዝምታውን ‹‹ከመንግስት ጋር እንደተስማማችሁ ያሳያል›› ሲሉ አዳራሹ በጩኸት ተሞልቷል፡፡ ‹‹እያንዳንዱ እጁን እያወጣ እንዲናገር መድረኩ ክፍት ነው›› ቢባሉም በግል የሚደርስባቸውን የቂም በቀል እርምጃ በመፍራት ሊናገሩ አለመፈለጋቸውን ገልፀውልናል ተሰብሳቢዎቹ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በየክልሉ ያሉ የማስታወቂያ ቢሮዎች ቢቻላቸው ስብሰባ እየጠሩ፣ ካልሆነ በስልክና በቃለ መጠይቅ አስተያየት እንዲሰበስቡ በታዘዙት መሰረት እየሰሩ ነው፡፡ እስካሁን በአማራ ክልል፣ በደቡብ ጉራጌ ዞን ወልቂጤና ቡታጅራ አስተያየቶች ተሰብስበው ወደ ቢሮ ገብተዋል፡፡ በተሰበሰበው አስተያየት መሰረት አብዛኛው ሰራተኛ በወ/ሪት ብርቱካን መታሰር እንደማይስማማ አሳውቋል፡፡ ‹‹አንድ ግለሰብ ተናገረ ተብሎ እየታሰረ እኛ እንዴት በነፃነት ሀሳብ መስጠት ይቻለናል፣ የህዝብ ንብረትና በርካታ ህይወት ያለፈበትን ጉዳይ በይቅርታ አልፌያለሁ ያለ መንግስት እንዴት ለንግግር ይቅርታ አነሰው፣ ህግን ማስከበር ከራስ ይጀምር፣ ቀጣዩ ምርጫ እንደ 97ቱ እንዳይሆን በፍርሀት የተወሰደ እርምጃ ነው›› የሚሉና ሌላችም አስተያየቶችን መሰብሰባቸውን የወልቂጤና ቡታጅራ ማስታወቂያ ቢሮ ባልደረቦች ይገልፃሉ፡፡ የመንግስትን እርምጃ የደገፉት አባላት ብቻ ናቸው ማለት ያስደፍራል የሚሉት እነዚሁ ምንጮች አለቆቻቸው የተሰበሰበውን አስተያየት ወደ አዲስ አበባ ለመላክ ስላልፈለጉ በሌላ ዙር ስብሰባ አስተያየቶችን ለመሰብሰብ አቅደዋል፡፡

ገዢው ፓርቲ ይህን ሁሉ አስተያየት እየሰበሰበ የሚገኘው ህዝብ በከፍተኛ ፀጥታ ውስጥ መግባቱ ስጋት ፈጥሮበት ነው፡፡ ባለፈው ምርጫ የተፈጠረውን ቀውስ ለማርገብ የወሰደው እርምጃ የአብዛኛውን ህዝብ ድጋፍ እንዲያጣ ያደረገው ኢህአዲግ የህዝብን ልብ አገኛለሁ ብሎ የልማት አርበኛ እያለ ገበሬ ቢሸልምም፣ ለወጣቶች ብድርና መሬት እየሰጠሁ ነው ቢልም ያለመውን ተቀባይነት ማግኘት አልተቻለውም፡፡ ‹‹ከአዲስ አበባ ህዝብ ጋር የፖለቲካ ጨዋታ አያዋጣም›› ብለው የተናገሩት ጠ/ሚ መለስ አሁን ደግሞ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር የፖለቲካ ፅብ ውስጥ መግባታቸውን የሚጠቁም እርምጃ መውሰዳቸውን የተረዱ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ያዘጋጁት ሰነድ ላይ ስብሰባው ያስፈለገው ‹‹የታሰበውን ያህል የህዝብ ድግፍ ባለማግኘቱ›› እንደሆነ መግለፁ ነው፡፡ በዚህ አካሄዳቸው ግን መቼም ቢሆን በህዝብ ተቀባይነት አያገኙም፡፡ የጠመንጃ አገዛዛቸው ይቀጥላል እንጂ፡፡

# እኛ ካልተነሳን ማን ? አሁን ካልተነሳን መቼ ?

## የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ !

በሚሊዮን የምንቆጠር ኢትዮጵያዉያን የምንወዳትን አገራችን እየተውን በስደቱ አለም እየኖርን ስንገኝ አብዛኞቻችን ለስደት የተዳረግነዉ በመልካም አስተዳደር ጉድለትና በኢኮኖሚ ችግር ነዉ።

ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በአገሩ ሰላምና ዲሞክራሲ ቢኖር ኖሮ መሰደድን አይመርጥም ነበር። የሰላምና የዲሞክራሲ አበባ ፈክቶ ኢትዮጵያ በፍቅርና በአንድነት የታነጸች አገር እንድትሆን የማይናፍቅና የማይመኝ ማንም ኢትዮጵያዊ የለም። የሁላችንም አላማና ግብ በዘር በኃይማኖት በጾታና በመደብ ያልተከፋፈለች፣ ሕግ የበላይ የሆነባትና የሰዉ ልጅ እንደስዕብናዉ የሚከበርባት አንዲት ኢትዮጵያን ማየት ነዉ።

ይች ሁላችንም የምንመኛት ኢትዮጵያ በቀላሉ፣ በጥቂቶች ጥረት ብቻ፣ ወይም በዝምታና በምኞችት አትገኝም። ይች ኢትዮጵያ የመለስ ዜናዊም ስጦታ አይደለችም።

ይችን ኢትዮጵያ ለማግኘት መስዋዕትነት መከፈል አለበት ። ይች ኢትዮጵያ እንድትኖር የማይፈልጉና ጥቅማቸዉ የሚነካባቸዉ ጥቂቶች፣ እኛ እንዳንቀሳቀስ ተስፋ እንድቆርጥና እንድንከፋፈል ለማድርግ ሌትህና ቀን መስራታቸዉ አይቀሬ ስለሆነ የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ ለማየት የነዚህን እኩይ ኃይላት ደባ ማክሸፍን ይጠይቃል።

ስለዚህ እያንዳንዳች ካቀረቀርንበት ቀና ብለን፣ የድርሻችንን ለማበርከት መዘጋጀት ይኖርብናል። እህታችን ሽብሬ ደሳለኝ እንዲሁም በሺሆች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን በየክልሉ ከአጋዚ ጦር በተተኮሰ ጥይት ወድቀዋል። እህታችን ብርቱካን ሚደቅሳ እኛ ሁላችንም ልናያት የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ ለማየት በመታገሏና «እምቢ ለባርነት» በማለቷ ከአምሳ ቀናት በላይ በግፍ በጨለማ ቤት ዉስጥ ከጠበቃዋ ጋር ሁሉ ሳይቀር እንዳትገናኝ ተከልክላ፣ ቶርቸር እየተደረገች ነዉ። ብዙ ኢትዮጵያዉያን ሕይወታቸው እየጠፋ፣ እየታሰሩ እየተደበደቡ ትዕግስት አስጨራሽ ትግል እያደረጉ ባሉበት ሁኔታ እኛ እጆቻችንን አጣምረን የምንቀመጥበት ጊዜ አይደለም።

በዉጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያዉያን በጥቃቅን ነገራት እግሮቻችን ተይዘዉ መጓዝ የነበረብንን ያህል አለመጓዛችን የታወቀ ቢሆንም ካለፉት ስህተቶች ተምረን በጋራ ከሰራን በወያኔ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማምጣት እንደምንችል አስረግጠን ማወቅ አለብን። በዉጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያ ትልቅ ኃያል አለን።

ሰላሳ በመቶ የዉጭ ምንዛሪ ወያኔ የሚያገኘዉ እኛ ዉጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያዉያን ከዉጭ ከምንልከዉ ዶላር ሲሆን አርባ በመቶ ደግሞ በልመና ከምዕራባዉያን አገራት የሚገኝ ነዉ። ስለዚህ ወያኔ ለግፍ አገዛዙ ከሚጠቀምበት ሰባ በመቶዉ የዉጭ ምንዛሪ ላይ እኛ በውጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያን ትልቅ ጫና ማድረግ እንደምንችል በግልጽ የሚያሳይ ነዉ።

እንግዲህ ይህን ያህል ኃይል እንዳለን ካወቅን ትንሽም ትሁን ትልቅ የድርሻችንን ከማበርከት ወደኋላ ማለት የለብንም። ከአቅማችን በላይ አይደለም። የአቅማችንንና የቻልነዉ በታማኝነትና ሳንጠይቅ ለአገራችን ለማበርከት መዘጋጀት ይኖርብናል። ስለምንስ አገራችን በተመለከተ እንለመናለን ? ስለምንስ እኛ ተኝተን ሌሎች እንዲሰሩ እንፈልጋለን ?

ዉድ ኢትዮጵያዉያን ልናበረክተዉ ከምንችላቸዉ በርካታ ነገራት አንዱና እጅግ በጣም ቀላሉ በሰላማዊ ስለፍ ተቃዉሞ ማሰማት ነዉ። ሰላማዊ ሰልፍ በርካታ ጥቅሞች አሉት። ከነዚህም መካከል በዋናነት የሚጠቀሱ ሁለቱ የሚከተሉት ናቸዉ፡

በዉጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያዊያን በአገራችን ላለው ሕዝብ ድምጽ ሆነን፣ ሲደማዉ ደምቶን፣ ሲያመዉ አሞን ተቃዉሞ ስናሰማ በኢትዮጵያ ላለዉ ወገናችን ትልቅ የሞራል ድጋፍ እንሆነዋለን። ሕዝባችንን ለማበረታት ሲባል ብቻ ሌላዉ ቢቀር እንኳን ሰልፍ መዉጣት ያስፈልጋል።

በሁለተኛነት የሚጠቀሰዉ የሰላምዊ ሰልፍ ጥቅም ወያኔ የምዕራባዉያንን ድጋፍ እንዲያጣ ስለሚረዳ ነዉ። ወያኔ ገንዘብ ለማግኘተ ራሱን እንደዲሞክራትና ሕግ አክባሪ አደርጎ የሚያቀርበዉን ማጭበርበር በማጋለጥ የበለጠ እርቃኑ እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል።

በተለይም ሰልፎች በተደጋጋሚ ከተደረጉና በርካታ ሕዝብ ከተገኘ መንግስታት የሚያራምዱትን ፖሊሲዎች እንዲመረምሩ የማድረግ ትልቅ አቅም አላቸዉ።

በአሜሪካን በቅርብ ስልጣን የጨበጡት ፕሮዜዳንት ባራክ ኦባማ የሰብዓዊ መብትን ከሚጥሱ፣ ሕግን ከሚረግጡና በሙስና ከተዘፈቁ ጋር አሜሪካ ዉል እንደማይኖራት በአዳባባይ ተናግረዋል። ወያኔ እንደለመደዉ መልኩን ቀይሮ እራሱን በኦባማ ፊት እንደ መልዓክ ለማቅረብ እየተፍጨረጨረ ባለበት ጊዜ እኛ ዝም ብለን ከተቀመጥን በቀላሉ የኦባማ አስተዳደር ባለሥልጣናትን ወደ እነርሱ ሊያመጡ እንደሚችሉ መዘንጋት የለብንም። ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያዉያን የኦባማ አስተዳደር የሕዝባችንን ብሶት እንዲያዉቅ የማድረግ አገራዊ ግዴታ አለብን።

በዚህ ምክንያት ከማርች 2 እስከ ማርች 9 2009 ባለዉ ሳምንት ዉስጥ በተለያዩ የአለም አቀፍ ከተሞች የአንድነት ድጋፍ ማህበራት ከኢሕአፓ ዲሞክራሲያዊ፣ ከሕብረት፣ ከኢትዮጵያ አገራዊ ጉባዔ፣ ከአዲሲቷ ኢትዮጵያ ሶሊዳሪቲ ንቅናቄ፣ ከኦሮሞ ተማሪዎች ሕብረትና ከጋሻ ኢትዮጵያ እንዲሁም ሌሌሎች የሲቪክና የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመሆን ሰላማዊ ሰልፍ ጠርተዋል።

በነዚህ ሰልፎች ኢትዮጵያዊያን የሆንን ሁሉ ተገኝተን የዜግነት ግዴታችንን እንድንወጣ ያስፈልጋል። ጊዜዉ የሥራ ጊዜ ነዉ። ጊዜዉ ከኢትዮጱያ ህዝብ ቆን ለኢትዮጵያ ደህንነት የምንቆምበት ጊዜ ነዉ። እኛ ካልተነሳን ማን ? አሁን ካልተነሳን መቼ ?

## ከወ/ሮ አልማዝ...

ከገጽ 2 የዞረ

ነች። የተገላቢጦሽ እኛን አይዟቹህ ትለናለች። እኔንም ሃሌንም እህቷንም ታጫወታለች። ታበረታታለች።

ደበበ - ሃሌ - ብርቱ ምን ትልሻለች ?

ወ/ሮ አልማዝ:- ሃሌ - እንዴት ነሽ ? አይዞሽ እመጣለሁ ትለኛለች። እንዴት ነሽ ስትለኝ ደህና ነኝ እላለሁ።

ደበበ - አባቷ ስለብርቱ ምን ይሉ ነበር ?

ወ/ሮ አልማዝ - አይ አይ እንኩዋንም ይህን አላዩ። አለማየታቸዉ እግዚአሄር ቢወዳቸዉ ነዉ። ችግሯን አይወዱም። ማንም ሲነካት አይፈልጉም። እንኳን ያላዩ ።

ደበበ - ይሄ አሁን የምንነጋገረዉ ዉጭ ያሉ ደጋፊዎች ጠይቀህ ላክልን ስላሉኝ ነዉ። ለነርሱ ምን የሚሏቸዉ ነገር አለ።

ወ/ሮ አልማዝ - በርቱልኝ ነዉ የምላቸዉ። «ከእግዚብሄር ጋር በርቱልኝ። ለምታደርጉት ነገር ሁሉ አመሰግናለሁ። እግዚአብሄር ከኔም ከናንተም ጋር ይሁን። እግዚአብሄር ከመላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ይሁን።» ነዉ የምለዉ። አመሰግናቹሃለሁ በብዙዉ በልልኝ።

ደበበ - ዉጪ ባሉት ደጋፊዎቻችንና በራሴም ስም በአንድነትም ስም ከልብ አመስግናለሁ።

አትላንታ * ቦስተን * ችካጎ * ዳላስ * ዴነቨር * ሎሳንጀለስ* ላስቬገስ * ሚኒያፖልስ * ናሽቪል * ኦክላነድ * ኦሃዮ * ፊኒክስ * ሳንሆዜ * ሲያትልን * ደቡብ ዳኮታ * አፕ ሰቴኢት ኒኦርክ * ዋሽንግትን ሜትሮ

ለአንድነት ለዲሞክራሲ ለፍትህ ፓርቲ ( ቅንጅት) በሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች መህበር
766 Rock Creek Church Rd., NW .Washington DC, 20010 *ስልክ (202) 541-0556
ፋክስ: (202) 541-0557.*ኢሜል: kinijitna@kinijitna.org
Www.kinijitna@kinijitna.org

አስተያየቶን በ awdethiopia@gmail.com ይጻፉልን